በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጋምቤላ ዩኒቨርስቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የጋምቤላ ዩኒቨርስቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ

ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የጋምቤላ ዩኒቨርስቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. በዉስጥ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በረዳት ገንዘብ ያዥ አቶ ዴንግ ጋች ከ2007 እስከ 2009 ዓ/ም ሲንቀሳቀስ የነበረዉ የሳጥን ገቢና ወጪ ሲመዛዘን ብር 759,774.00 በማነስ የታየ ሲሆን ገንዘቡ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
2. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሶስት ገንዘብ ያዡች እጅ በቆጠራ የተገኘው የጥሬ ገንዘብና ሰነድ ድምር ብር 20,338.50 ሲሆን በተቀጽላ ሌጀሮች 001፣ 002 እና 003 በእጅ ባለ ጥሬ ገንዘብ በሳጥን ሂሳብ (የሂሳብ መደብ 4101) በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገው ብር 2,591,346.74 በመሆኑ በሪፖርት የተመለከተው በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ በብልጫ ወይም በገንዘብ ያገዦች እጅ በቆጠራ የተገኘው በማነስ ብር 2,571,008.24 የሚያሳይ መሆኑ፣ በተጨማሪም ይህ ልዩነት በ2008 በጀት ዓመት በሁለት ተቀጽላ ሌጀሮች (ተቀጽላ ሌጀር 001 እና 002) ብር 2,175,405.11 የነበረ ሲሆን ይህ ሳይስተካከል በዚህ በጀት ዓመት ልዩነቱ በብር 395,603.13 (2,571,008.24-2,175,405.11) ከፍ ያለ መሆኑ፣
3. በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለትአንቀፅ 7 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ ላይ በአገር ዉስጥ ገንዘብ ለሚሰበሰብ ገቢ የገቢ ደረሰኝ መሂ/1 ወይም ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ በሚታተም ደረሰኝ ብቻ መሆን

እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው ከሐምሌ 1/2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ባለው ጊዜ ዉስጥ (በ2009 የበጀት ዓመት) በገቢ ሂሳብ ሂሳብ መደቦች 1443 እና 1489 ብር 4,623,489.88 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ የሰበሰበ መሆኑ፣

4. የቀድሞ ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር (ያሁኑ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር) በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ ‹‹በስራ አመራር ቦርድ የሚመሩ አንዳንድ የከፍተኛ ትምህርት እና ሌሎች ተቋማት ከመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ውጪ የሰራተኞችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች ለሥራ አመራር ቦርድ እያቀረቡ በማስወሰን ተግባራዊ ማድረጋቸውን በመገንዘብ፣ ጉዳዩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ4ኛው የምርጫ ዘመን 15ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ ተነስቶ ውይይት ከተደረገ በኋላ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ፈቃድ ውጪ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከአሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ሲል በጥብቅ ያሳሰበ ቢሆንም በድምሩ ብር 135,000.00 ለዘጠኝ (9) አመታዊ እቅድ ላዘጋጁ የኮሚቴ አባላት እና ስትራቴጂክ እቅድ ላዘጋጁት የዩንቨርሲቲው መምህራን ለማበረታቻ አበል በሚል የተከፈለ መሆኑ፣

5. የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9/3 ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ተገለጸ ቢሆንም ለመኪና ጥገና ለኢትዮ ኒፖን አክ/ማህበር ለተከፈለ ብር 69,683.18 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ከወጪ ማስመስከሪያው ጋር ባለመያያዙ የተፈጸመዉ ክፍያ ዩንቨርሲቲዉ ላገኘዉ አገልግሎት መሆኑን ለማረጋገጥ ሳይቻል መቅረቱ፣

6. በኢትዮጵያፌደራላዊ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ የመንግስት መስሪያ አሸናፊዉን ተጫራች ለመምረጥ በጫረታ ሰነዱ በተመለከተዉ የግምገማ መስፈርት መሰረት ተፈላጊዉን ያሟላ የመጫረቻ ሰነዶችን መገምገምና ማወዳደር እንዳለበት እና በጫረታ ሰነዱ ላይ ያልተመለከተ የማወዳደሪያ መስፈርት በጥቅም ላይ ሊዉል እንደማይችል የተደነገገ ቢሆንም፤ በአቃላይ ለግዥዎች ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ አቅራቢዎች እያሉ ግዥዎቹ

ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡት በመፈጸማቸው በድምሩ ብር 131,671.15 ተጨማሪ ወጪ እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ፣

7. የወጪ ሂሳቦች የተያዙትና የተመዘገቡት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የተከታታይ ርቀት ት/ት ፕሮግራም ላስተማሩት ለሠራተኞች ጥቅማጥቅም የከፈለ ብር 280,040.00 ሠራተኞች ለሚሰጡት አገልግሎት ሂሳብ (በሂሳብ መደብ 6116) መያዝ ሲገባ በምግብ ሂሳብ (በሂሳብ መደብ 6216) ተይዞ መመዝገቡ፣
8. እስከበጀት ዓመቱ መጨረሻ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደና በሂሳብ መደቦች 4201፣ 4203፣ 4210 እና 4211 የተያዘ በድምሩ ብር 3,298,500.98 ተሰብሳቢ እንዲሁም በሂሳብ መደብ 5004 የተያዘ ብር 3,124,164.23 ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣
9. ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር **36,092,729.98** በወጪ ሂሳብ መደቦች 6111፣ 6113፣ 6121፣ 6123፣ 6131፣ 6133፣ 6212፣ 6218፣ 6219፣6232፣ 6233፣ 6256፣ 6258፣ 6259 እና 6313 የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው የተስተካከለ በጀት በላይ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ፣ ከዚህ ውስጥ በወጪ ሂሳብ መደብ 6123 የወጣ ብር 387,440.33 እና በወጪ ሂሳብ መደብ 6256 የወጣ ብር 59,973.52፣ በድምሩ ብር 447,413.85 አስቀድሞ በጀት ባልጸደቀባቸው /ባልተፈቀደባቸው ወይም በጀት በሌላቸው/ የወጪ ሂሳብ መደቦች ወጪ የተደረገ መሆኑ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሣብ መግለጫዎች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፣ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)

1. የዩኒቨርሲቲው ፋይናንስ ክፍል በገንዘብ ያገሮች በሚጠበቀው ካዝና ውስጥ የሚገኘውን ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርግ እና የገንዘብ ያገሮች የጥሬ ገንዘብ ሌጀር ከሚያሳየው ከወጪ ቀሪ ጋር በማመሳከር የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ መግለጫ የማያዘጋጅ መሆኑ፣

2. ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 19,178,605.94 በወጪ ሂሳብ መደቦች 6112፣ 6114፣ 6211፣ 6213፣ 6214፣ 6216፣ 6217፣ 6221፣ 6222፣ 6223፣ 6231፣ 6243፣ 6244፣ 6245፣ 6251፣ 6252፣ 6253፣ 6254፣ 6255፣ 6257፣ 6271፣ 6323፣ 6412፣ 6414፣ 6417 እና 6419 ከተመደበው የተስተካከለ በጀት በየሂሳብ መደቡ ከ10% በላይ ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣

<u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

<u>ንብረት</u>

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂና የቋሚ ንብረቶች ከወጪ ቀሪ ቆጠራ (Inventory) ያልተደረገ መሆኑ፤
- በዩንቨርሲቲው የአላቂ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ቋሚ እቃዎች፣ በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አላቂ እቃዎች የሚገኙ መሆናቸዉ፣
- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ አገልግሎት አይሰጡም ተብለዉ የተመለሱ የተለያዩ ላፕቶፖች (ብዛት 5) ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸዉ፣
- በዩኒቨርሲቲ ግቢ ዉስጥ ያለአገልግሎት የተቀመጠ ጄኔሬተር መኖሩ፣
- በንብረት ስቶር ዉስጥ መወገድ የነበረባቸው ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ የተለያዩ የመኪና ጎማዎች ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆናቸዉ፣ በዩኒቨርሲቲ ግቢ ዉስጥ የተለያዩ ቦታዎችና ወደ ምግብ ቤት አከባቢ መወገድ የነበረባቸው ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ የብረት አልጋዎች፣ሳጥኖች፣ቆርቆዎች እና ወንበሮች ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆናቸዉ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

<u>የተማሪዎች ክሊኒክ፣</u>

- በተማሪዎች ክሊኒክ ስቶር ገቢና ወጪ ለሚደረጉ መድሃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- በበጀት አመቱ መጨረሻ በተማሪዎች ክሊኒክ ስቶር እንዲሁም በህክምና መስጫ የሚገኙ መድሃኒቶች ቆጠራ እና ከወጪ ቀሪ የሚያሳይ ሪፖርት (reconciled report) የሌለ መሆኑ፤
- በዕርዳታ የተገኙ የቲቢና የወሊድ መከላከያ መድሃኒቶች ዋጋቸዉ ሳይጠቀስ ገቢ የሚደረጉ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ክሊኒክ ውስጥ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸዉ መድሃኒቶች ሳይወገዱ ተከማችተዉ የተቀመጡ መሆኑ፣

የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ፣

- የሰሌዳ ቁጥር ኢ.ት 4-08711 Mercedes Bus እና የሰሌዳ ቁጥር ኢ.ት 4-05683 ኤኔትሬ፣ በድምሩ 2 ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ መከታተያ የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ እና ተሸከርካሪዎቹ በሂዱበት ኪ/ሜ ተገምቶ ነዳጅ የሚሞላላቸው መሆኑ፣
- የሰሌዳ ቁጥር ኢ.ት 4-05683 ኤኔትሬ (**እላይ ጌጁ የማይሠራ የተባለ**) እና ሰሌዳ ቁጥር ኢ.ት 4-16861 ኒሳን፣ በድምሩ 2 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ፣

ልዩ ልዩ፣

- በዩንቨርሲቲዉ በጥበቃ፣ በግዥ፣ በንብረት ያዥነት እንዲሁም በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 አንቀጽ 7 መሰረት ዋስትና እንዲያቀርቡ መደረግ ሲገባ የተወሰኑት ያለምንም ዋስትና እየሰሩ መሆኑ፣
- የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የሰው ኃይል ሁኔታ ሲታይ፣ ለዳይሬክቶሬቱ 10 ኦዲተሮች የሚያስፈልጉ ቢሆንም ለክፍሉ አንድ ኦዲት ዳይሬክተር እና አንድ የፋይናንስ ኦዲት ቡድን መሪ ባለሙያዎች ብቻ የተቀጠሩ ሲሆን በ8 ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኛ ያልቀጠረ በመሆኑ 80 በመቶ የክፍሉ የሰው ኃይል ያልተሟላ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ለተልዕኮው መሳካት በሚያከናውናቸው ቁልፍ ተግባሮች ላይ በመመርኮዝ እና በሚያከናውናቸው የዕለት ተዕለት ሥራዎች ውስጥ እንደ ግዥና ንብረት አስተዳደር፣ ፋይናንስ አስተዳደር፣ ምግብ አገልግሎት፣ ነዳጅ እደላ እና በመሳሰሉት ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶችን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚረዱ የአሰራር ስልቶችን በመቀየስ የዩኒቨርሲቲውን የስጋት ተጋላጭነት አስተዳደር ዕቅድ /Risk Management Plan/ የሌለው መሆኑ፣

እርምጃ ያልተወሰደበት የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝትና የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ለተሽከርካሪ ጥገና ለተከፈለ ብር 24,818.75 እና የጤፍ ዱቄት ለተገዛበት ብር 244,598.00፣ በድምሩ ብር 269,416.75 (24,818.75 + 244,598.00) ገንዘቡን ከተቀበሉ ድርጅቶች የቀረቡ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች ከወጪ ሰነዶቹ ጋር ያልተያያዙ መሆኑ፣
- በዩንቨርሲቲዉ በጥበቃ፣ በግዥ፣ በንብረት ያዥነት እንዲሁም በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች በመመሪያዉ መሰረት ዋስትና እንዲያመጡ ወይም እንዲያቀርቡ መደረግ ሲገባ ያለምንም ዋስትና እየሰሩ መሆኑ፣

በሚሉ ግኝቶች ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀትዓመት ሂሳብ ኦዲትግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓለማ

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በጋምቤላ ዩኒቨርስቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ</u>፣

1.1 <u>ግኝት</u>፣

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በአግባቡ ተመዝግቦ የሚያዝ መሆኑን እንዲሁም የሳጥን ሌጀር ሚዛን እና በሳጥን ተገኝቶ የተቆጠረን ጥሬ ገንዘብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በዉስጥ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በረዳት ገንዘብ ያዥ አቶ ዴንግ ጋች ከ2007 እስከ 2009 ዓ/ም ሲንቀሳቀስ የነበረዉ የሳጥን ገቢና ወጪ ሲመዛዘን ብር **759,774.00** በማነስ የታየ ሲሆን ገንዘቡ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሶስት ገንዘብ ያዦች እጅ በቆጠራ የተገኘው የጥሬ ገንዘብና ሰነድ ድምር ብር 20,338.50 ሲሆን በተቀጽላ ሌጀሮች 001፣ 002 እና 003 በእጅ ባለ ጥሬ ገንዘብ በሳጥን ሂሳብ (የሂሳብ መደብ 4101) በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገው ብር 2,591,346.74 በመሆኑ በሪፖርት የተመለከተው በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ በብልጫ ወይም በገንዘብ ያገሮች እጅ በቆጠራ የተገኘው በማነስ ብር 2,571,008.24 የሚያሳይ መሆኑ፣ በተጨማሪም ይህ ልዩነት በ2008 በጀት ዓመት በሁለት ተቀጽላ ሌጀሮች (ተቀጽላ ሌጀር 001 እና 002) ብር 2,175,405.11 የነበረ ሲሆን ይህ ሳይስተካከል በዚህ በጀት ዓመት ልዩነቱ በብር 395,603.13 (2,571,008.24-2,175,405.11) ከፍ ያለ መሆኑ፣
- የዩኒቨርሲቲው ፋይናንስ ክፍል በገንዘብ ያገሮች በሚጠበቀው ካዝና ውስጥ የሚገኘውን ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርግ እና የገንዘብ ያገሮች የጥሬ ገንዘብ ሌጀር ከሚያሳየው ከወጪ ቀሪ ጋር በማመሳከር የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ መግለጫ የማያዘጋጅ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

1.2 <u>ስጋት</u>፣

በየወሩ አሊያም በአንድ በተወሰነ ወቅት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በማድረግ በሌጀር ከተመለከተው ከወጪቀሪ ጋር በማመሳከር (በማመዛዘን) ውጤቱ እንዲታወቅ አለማድረግ ጉድለት እንኳን ቢከሰት በወቅቱ እርምጃ ለመውሰድ አያስችልም፡፡

1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የመንግሥትን ገንዘብ ከጥፋትና ከጉድለት ለመከላከል እንዲቻል ከላይ በተጠቀሱት የአሠራርና የቁጥጥር ግድፈቶች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ፣ በልዩነት የታየው ብር 759,774.00 ለመንግሥት /ለዩኒቨርስቲው/ ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደሩ የመንግሥት ደንብና መመሪያን ተከትሎ እንዲፈጸም የሥራ አመራሩ ጉዳዩ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል በጥብቅ በማስገንዘብ አፈጻጸሙንም መከታተል ይኖርበታል፡፡

1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ፣

- በረዳት ገንዘብ ያዥ አቶ ዴንግ ጋች ከ2007 እስከ 2009 ዓ/ም ሲንቀሳቀስ የነበረዉ የሳጥን ገቢና ወጪ ሲመዛዘን በማነስ የታየው ግለሰቡ በህግ ቁጥጥር ስር ውሎ ጉዳዩ በመታየት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ውሳኔ እንዳገኘ የሚያሳውቁ መሆኑን፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሶስት ገንዘብ ያዞች እጅ በቆጠራ የተገኘው የጥሬ ገንዘብና ሰነድ በሪፖርት ከታየው በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ በብልጫ ወይም በገንዘብ ያገሮች እጅ በቆጠራ የተገኘው በማነስ የታየው በቀጥታ ከክልሉ ፋይ/ኢኮ/ትብ/ ቢሮ ትብብር በመጠየቅ የኦዲት ሥራ ያስጀመሩ በመሆኑ ይህ እንደተጠናቀቀ ሪፖርት የሚያደርጉ መሆኑን፤
- ከ2007 እስከ 2009 ዓ.ም የቀን ገቢ እና ወጪ በጥሬ ገንዘብ መዝገብ (cash book) ላይ ያለመጠቀም እና ያለመመዝገብ ችግር የመነጨው በአሰራር ስህተት በመሆኑ በዚህ ረገድ የነበረባቸውን ችግር በመጠኑም ቢሆን ከ2010 የበጀት ዓመት ጀምሮ ማስተካከላቸውን፣ በዚሁ መሠረት ታይቶ የነበረው የጥሬ ገንዘብ ልዩነት በፍትሀብሔር እየታየና ተጣርቶ ሲጠናቀቅ ለሚመለከተው አካል በፍጥነት ሪፖርት የሚያቀርቡ እንደሚሆን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

2.1 <u>የገቢ ሂሳብ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ የሚሰበሰብ ስለመሆኑ፣</u>

2.1.1<u>ግኝት፣</u>

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለትአንቀፅ 7 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ ላይ በአገር ዉስጥ ገንዘብ ለሚሰበሰብ ገቢ የገቢ ደረሰኝ መሂ/1 ወይም ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ በሚታተም ደረሰኝ ብቻ መሆን እንዳለበት ተገልጿል፡፡

በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፣ ዩኒቨርሲቲው ከሐምሌ 1/2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ባለው ጊዜ ዉስጥ (በ2009 የበጀት ዓመት) በገቢ ሂሳብ ሂሳብ መደቦች 1443 እና 1489 ብር 4,623,489.88 የሰበሰበ ቢሆንም ሂሳቡ የተሰበሰበው በሂሳብ አያያዝ መመሪያው መሰረት በገቢ ደረሰኝ ሳይሆን በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

2.1.2 <u>ስጋት</u>፣

የመንግስት ገንዘብ ከመንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ዉጪ ከተሰበሰበ ለጥፋትና ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

- ዩኒቨርሲቲው ማንኛውንም ገቢውን እና ወጪውን በህጋዊ የሂሳብ ምዝገባ ቫውቸሮች ማከናወን ይኖርበታል፡፡
- የዩኒቨርሲቲው ገቢ በመግስት ሂሳብ አያያዝ መሰረት ተመዝግቦ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

የሥራ አመራሩ፣

- በሰው ቅጥር በኩል የክልሉ እና የዩኒቨርስቲው የተፈላጊ ችሎታ የአቀጣጠር መመሪያ በመለያየቱና በክልሉ ከፌዴራሉ በአነሰ የሥራ ልምድና የትምህርት ደረጃ ስለሚቀጥር ዩኒቨርሲቲው በፋይናንስ ዘርፍ ብቃት ያለውና የሰለጠነ ባለሙያ ማግኘት ባለመቻሉ ይህ ችግር መፈጠሩን ጠቅሰው ይህ ቢሆንም የሚሰበሰቡት የውስጥ ገቢ በባንክ አካውንታቸው የሚገባና በቦርድ አስፀድቀው ሥራ ላይ ያዋሉ ሲሆን አፈጻጸሙንም ለፌዴራል ገን/ኢ/ት/ብ/ሚ/ ሲያሳውቁ የነበረ ሲሆን በ2010 የበጀት ዓመት ዳግም ስህተት እንዳይፈጠር በተቻለ መጠን የተወሰነ ባለሙያ ከሥራ ገበያ ቦታው ላይ የመደቡ በመሆኑ ማንኛውም የውስጥ ገቢ የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ እንዲቀምስ የማድረግ ሥራ መጀመሩን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3. <u>የወጪ ሂሳብ</u>፤

ለተለያዩ አገልግሎቶች የዋለው የወጪ ሂሳብ በፌዴራል መንግስት ታምኖበት በወጡ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈጸሙን እንዲሁም ለማንኛውም ክፍያ የተሟላ ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎች የቀረቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱ ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

3.1 አላግባብ የተከፈለ ጥቅማ ጥቅም፣

3.1.1 ግኝት፤

የቀድሞ ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር (ያሁኑ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር) በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ላይ ‹‹በስራ አመራር ቦርድ የሚመሩ አንዳንድ የከፍተኛ ትምህርት እና ሌሎች ተቋማት ከመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ውጪ የሰራተኞችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች ለሥራ አመራር ቦርድ እያቀረቡ በማስወሰን ተግባራዊ ማድረጋቸውን በመገንዘብ፣ ጉዳዩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ4ኛው የምርጫ ዘመን 15ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ ተነስቶ ውይይት ከተደረገ በኋላ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ፈቃድ ውጪ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና እስከአሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ሲል በጥብቅ ባሳሰበው መሰረት ስለመከናወኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በናሙና ኦዲት ከተደረጉት ውስጥ፤

ዝርዝር ሁኔታው	ቀን	የሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	ገንዘቡን የተቀበሉ	የገንዘቡ ልክ
የ2010 ዓ/ም አመታዊ እቅድ ላዘጋጁት የኮሚቴ አባላት	12/10/2009	261918	ለመምህር እንዳልከካቸዉ ታዬ	15,000.00
	12/10/2009	261917	ለመምህር ጌታቸዉ በቀለ	15,000.00
	12/10/2009	261919	መምህር ዘገየ ሙሉ	15,000.00
	12/10/2009	261920	ለአቶ ዲንቁሳ እንኮሳ	15,000.00
የዩንቨርሲቲዉን ስትራቴጂክ እቅድ ላዘጋጁት	13/10/2009	261939	ለመምህር ጀምበሩ አለሙ	15,000.00
	13/10/2009	261940	ለመምህር ታምራት ዲና	15,000.00
	13/10/2009	261937	ለአቶ ኡቻን ኡኬሎ	15,000.00
	13/10/2009	261938	ለመምህር ኡዋር ቶነ	15,000.00
	13/10/2009	261935	ለመምህር አብዮት ማሞ	15,000.00
			ድምር	**135,000.00**

በድምሩ ብር 135,000.00 ለዘጠኝ(9) አመታዊ እቅድ ላዘጋጁት የኮሚቴ አባላት እና ስትራቴጂክ እቅድ ላዘጋጁት የዩንቨርሲቲው መምህራን ለማበረታቻ አበል በሚል አላግባብ ከመመሪያ ዉጪ የተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

3.1.2 <u>ስጋት</u>፣

ዩኒቨርስቲዉ መንግሥት ያወጣቸዉን ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ የማይሰራ ከሆነ የመንግሥትን ንብረት አላግባብ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡ ለወደፊቱም እንዲህ አይነት ክፍያ የሚቀጥል ከሆነ የመንግሥት ገንዘብ ለበለጠ ብክነት ይጋለጣል፡፡

3.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

የዩኒቨርሲቲዉ አስተዳደር በመንግስት የወጡ ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና አዋጅ በተገቢዉ ተግባራዊ ለመሆኑ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም አለአግባብ ከመንግስት መመሪያ ዉጭ የተከፈለ የማበረታቻ ክፍያ ተገቢ ባለመሆኑ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ፣

- የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ውስጥ በቂ የሰው ሀይል በገበያ ላይ ባለማግኘቱ ምክንያት በርካታ መደቦች በክፍትነት የሚገኙ መሆናቸውን ይህም በአሰራራቸው ላይ ችግር መፍጠሩን በተደጋጋሚ ለኢፌዲሪ የፐብ/ሰር/የሰው ሃብ/ልማ/ሚኒስቴር አሳውቀው መፍትሄ ባለመገኘቱ በአስተዳደር መደብ ላይ ያለውን ክፍተት ለመሸፈንና ስራ እንዳይበደል ሲባል ስትራቴጂክ ዕቅድ ሆነ ሌሎች ወሳኝ ሥራዎችን ብቃትና ጥራት ባላቸው መምህራን ከትምህርት ሰዓት ውጪ እንዲያከናውኑላቸው ውል በማስገባት በትርፍ ጊዜያቸው ያዘዙት እንጂ ለማበረታቻ ባለመሆኑ ለማበረታቻ የተባለው አገላለጽ በስህተት የተጠቀሙ መሆኑ ታውቆ በዚህ እንዲስተካከልላቸውና ይህንንም ያደረጉት በማናጅመንት በማስወሰን መሆኑን ጠቅሰው ለወደፊቱ የሰው ኃይላቸውን ካሟሉ ተመሳሳይ ድርጊት የማይፈጽሙ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ይህ እንደመደበኛው ሥራ መሠራት ያለበት በመሆኑ በመምህራን ለማሠራት ቢፈለግም በቁርጥ ተመን ከመክፈል ሁኔታው ታይቶ ጊዜ ካላቸው መንግሥት በየደረጃው በፈቀደው የመምህራን የትርፍ ሰዓት አከፋፈል መሠረት በተፈቀደላቸው

ክሬዲት ሀወር መሆን ስለነበረበት የተሰጠው ምላሽ አሳማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

3.2.1 <u>ግኝት፣</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ ተራ ቁጥር 9 አንቀጽ 3 ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች፣ ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ይገልጻል፡፡

የዩኒቨርስቲዉ ክፍያ በዚህ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በቀን 23/03/2009 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 141435 ለመኪና ጥገና ለኢትዮ ኒፖን አክ/ማህበር የተከፈለ ብር 69,683.18 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ከወጪ ማስመስከሪያው ጋር ባለመያያዙ የተፈጸመዉ ክፍያ ዩንቨርሲቲዉ ላገኘዉ አገልግሎት መሆኑን ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

3.2.2 <u>ስጋት፣</u>

ዩኒቨርሲቲው አስፈላጊዉ የወጪ ማስረጃ ሳይሟላ ክፍያ የሚፈጽም ከሆነ የክፍያዉን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ለሂሳቡ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እንዲቀርብ ወይም ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ለወደፊቱም የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት አስፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የኢትዮ-ኒፖን ካምፓኒ አክስዮን ማህበር ለማሰራት የተላከው ፓጃሮ መኪና ቅድመ ክፍያ ስለተጠየቀ በካምፓኒው አካውንት ያስገቡ ቢሆንም ተሽከርካሪው ተጠግኖ ሲመጣ ዋና የሽያጭ ደረሰኝ ሳይላክ መቅረቱ ስህተቱን በመቀበል በቀጣይ በአጭር ጊዜ ዋናውን የሽያጭ ደረሰኝ ከካፓኒው አስመጥተው ከወጪ ሠነዱ ጋር የሚያያይዙ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.3.1 <u>ግኝት፣</u>

በኢትዮጵያፌደራላዊ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቱ በዚሁ አዋጅና አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 በተደነገገዉ መሰረት አሸናፊዉን ተጫራች ለመምረጥ በጫረታ ሰነዱ በተመለከተዉ የግምገማ መስፈርት መሰረት ተፈላጊዉን ያሟላ የመጫረቻ ሰነዶችን መገምገምና ማወዳደር እንዳለበት እና በጫረታ ሰነዱ ላይ ያልተመለከተ የማወዳደሪያ መስፈርት በጥቅም ላይ ሊዉል እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሰረት መመሪያው በዩኒቨርሲቲው መተግበሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በናሙና ኦዲት ከተደረጉት ውስጥ ቀጥሎ የተመለከተው ሁኔታ ተገኝቷል፡፡

የምግብአ ይነት	ቀን	የባንክወጪ ማሰመስከሪ ያቁጥር	የሂሳብመደ ብ	የአቅራቢዎችስምዝርዝርእናያቀረቡትየአንድኪሎዋጋ				
				ሳምሶንአላዘር	በህሩናስንታዮ	ተከላይግዳይ	ብዛት	የዋጋ ልዩነት
ምስርክክ	28/06/09	141271	6216	72,000.00(60*1200)	59,268.00(49.39*1200)	-	1200	12,732.00
ሽሮ	28/06/09	141271	6216	45,600.00(38*1200)	-	39,600.00 (33*1200)	1200	6,000.00
ፓስታ	28/06/09	141271	6216	28,800.00(36*800)	16,080.00(20.10*800)	-	800	12,720.00
ምስርክክ	23/10/09	141029	6216	36,000.00(600*60)	29,634.00(600*49.39)	-	600	6,366.00
ሽሮ	23/10/09	141029	6216	26,600.00(700*38)	-	23,100.00 (700*33)	700	3,500.00
ፓስታ	23/10/09	141029	6216	27,000.00(750*36)	15,075(750*20.10)	-	750	11,925.00
ምስርክክ	19/03/09	141411	6216	90,000.00(1500*60)	74,085.00(1500*49.39)	-	1500	15,915.00
ሽሮ	19/03/09	141411	6216	70,300.00(1850*38)	-	61,050.00 (1850*33)	1850	9,250.00
ፓስታ	19/03/09	141411	6216	45,000.00(1250*36)	25,125.00(1250*20.10)	-	1250	19,875.00
ቅንጨ	19/03/09	141411	6216	32,200.00(1150*28)	-	28,750.00 (1150*25)	1150	3,450.00
ምስርክክ	25/05/09	261828	6216	54,000.00(900*60)	44,451.00(900*49.39)	-	900	9,549.00
							ድምር	**111,282.00**

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተመለከተው ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢ የሆኑት የጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴ ያወጣዉን የማወዳደሪያ መስፈርቱን የማያሟሉ ስለመሆኑ ሳይገለፅ ከፍተኛ

ዋጋ አቅራቢ የሆኑት ድርጅቶችን አሸናፊ በማድረግ ተጨማሪ ወጪ ብር **111,282.00** እንዲወጣ የተዳረገ መሆኑ፣

- በተጨማሪም በቀን 26/10/2009 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 277451 ብር 457,141.85 ለሳሙኤል እንዳለ የልብስ ስፌት ንግድ ድርጅት ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ከተገዙት ጋዎኖች ዉስጥ፣
    - ➢ ለማስተርስ ጋዎን ስፌት ሳሙኤል እንዳለ የልብስ ስፌት ንግድ ድርጅት ለያንዳንዱ ብር 850.00 እና ለ50 ጋዎን ብር 42,500.00 (50*ብር 850.00) ዋጋ ፀጋዬ ብርኃኔ ደግሞ ለያንዳንዱ ብር 590.00 እና ለ50 ጋዎን ብር 29,500.00 (50*ብር 590.00) እንዲሁም፣
    - ➢ ለፒ.ኤች.ዲ ጋዎን ስፌት ሳሙኤል እንዳለ የልብስ ስፌት ንግድ ድርጅት ለእያንዳንዱ ብር 1,150.00 እና ለ15 ጋዎን ብር 16,650.00 (15*ብር 1,110.00) ዋጋ ፀጋዬ ብርኃኔ ደግሞ ለያንዳንዱ ብር 617.39 እና ለ50 ጋዎን ብር 9,260.85 (15*ብር 617.39) ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ ሲሆን፣

ግዥው ግን አለአግባብ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ከሳሙኤል እንዳለ የልብስ ስፌት ንግድ ድርጅት የተፈጸመ በመሆኑ ብር 20,389.15 ተጨማሪ ወጪ እንዲወጣ የተዳረገ መሆኑ፣

በአቃላይ ለግዥዎች ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ አቅራቢዎች እያሉ ግዥዎቹ ግን ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡት በመፈጸማቸው በድምሩ ለብር 131,671.15 (111,282.00+20,389.15) ተጨማሪ ወጪ እንዲወጣ የተዳረገ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

3.3.2 <u>ስጋት</u>፣

- አስፈላጊነታቸው በመንግስት ታምኖበት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መተላለፍ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ዩንቨርሲቲዉ ለተጨማሪ ወጪ እንድጋለጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

3.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በመሆኑም ከአዋጁ ውጪ ለተፈጸመዉ ግዥና አላግባብ ለወጣዉ ገንዘብ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶ ሪፖርት ሊቀርብ እና ለወደፊቱም በዚህ ረገድ ጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል፡፡

3.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ፣

- ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት ለተማሪዎች ቀለብ አገልግሎት የሚውል የተለያዩ የምግብ አይነቶችን በተለያዩ ሎት በማከፋፈል በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በግልፅ ጨረታ በማወደደር አሸናፊዎች በመለየት ግዥ መፈጸሙ የሚታወቅ ሲሆን በኦዲት ግኝቱ እንደተገለፀው በሎት 5 የጥራጥሬ እህሎች ከየዝርዝር የጥራጥሬ እህሎች ላይ በኦዲት ግኝቱ ላይ የተዘረዘሩ ምንም እንኳ በምስር ክክ፣ ሽሮ፣ ፓስታ፣ ቅንጨ በውድድሩ የቀረቡ የተለያዩ ተጫራቾች በእያንዳንዱ የጥራጥሬ እህል ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ ቢሆኑም የግዥ ኮሚቴው ለአቅርቦት አመቺ እንዲሆን፣ በወር የሚቀርበው መጠን አነስተኛ በመሆኑ በእያንዳንዱ የጥራጥሬ እህሎች አሸናፊ ቢደረግ በውል ላይ አቅራቢዎች ፍቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ በሚል ስጋት በግምገማ ወቅት በእያንዳንዱ የጥራጥሬ እህል ሳይሆን በየሎት ዝርዝር ድምር በማድረግ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች አሸናፊ እንዲሆን መደረጉን ጠቅሰው፣ ከዚህ ግኝት ትምህርት በመውሰድ በ2010 በጀት ዓመት በተካሄደው የተማሪዎች ምግብ ጨረታ ምንም እንኳን በሎት ቢወዳደሩም በያንዳንዱ ዓይነት በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢ እንዲያቀርብ በማድረግ ማሻሻያ ማድረጋቸውን፣
- ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት ለተማሪዎች ለመመረቂያ አገልግሎት የሚውል 1000 የመጀመሪያ ድግሪ ጋዎን፣ 50 የማስተርስ ጋዎን እና 15 የፒኤችዲ ጋዎን በግለፅ ጨረታ በማውጣት ማወዳደራቸው የሚታወቅ ሲሆን በውድድር ወቅት ከነበሩ አቅራቢዎች (ተጫራቾች) ሁለት ተጫራቶች የተሟላ መስፈርቶችን ያሟሉ ሲሆኑ የግዥ ክፍሉ በግምገማ ወቅት ዋጋን ብቻ ሳይሆን በበለጠ ትኩረት የተሰጠው ያቀረቡትን ናሙና (ሳምፕል) ሲሆን ያቀረቡትን ድምር የሎት ዝቅተኛ ዋጋ እና የናሙና ጋዎን ጥራት፣ የጋዎኑን ዲዛይን ግምት ውስጥ በማስገባት ምንም እንኳን የአቶ ብርሃኔ ፀጋዬ የማስተርስ ጋዎን እና የፒኤችዲ ጋዎን ዝቅተኛ ዋጋ ቢያቀርቡም የአቶ ሳሙኤል አንደኛ በብዛት የድግሪ ስለሚፈለግ በድግሪው ጋዎን ተመጣጣኝ ዋጋ እና የተፈለገ ናሙና የዩኒቨርስቲውን መምህራን በማስመረጥ እንዲሁም ከዚህ በፊት በዘርፉ የነበራቸውን የአቅርቦት ልምድ ግምት ውስጥ በማስገባት የማስተርስ እና የፒኤች ዲ ጋዎን ያቀረቡት ናሙና ከአቶ ብርሃኔ ፀጋዬ ያቀረቡት ናሙና ሲነፃፀር

የበለጠ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ የጋዎኖችን ሎት ድምር በማነፃፀር ዝቅተኛ ዋጋ እና ጥራት በማየት አቶ ሳሙኤል እንዳለ አሸናፊ እንዲሆኑ መደረጉን፣

በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

3.3.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ውድድር ሲደረግ ዝቅተኛ ዋጋ በሎት ሳይሆን በየዕቃው ተለይቶ መታየት ያለበት በመሆኑና የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ባለመሆኑ በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

3.4.1 <u>ግኝት</u>፣

የወጪ ሂሳቦች የተያዙትና የተመዘገቡት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ዩኒቨርሲቲዉ በቀን 10/09/2009 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 141190 ተከታታይ ርቀት ት/ት ፕሮግራም ላስተማሩት ለሠራተኞች ጥቅማጥቅም የከፈለ ብር 280,040.00 ሠራተኞች ለሚሰጡት አገልግሎት ሂሳብ (በሂሳብ መደብ 6116) መያዝ ሲገባ በምግብ ሂሳብ (በሂሳብ መደብ 6216) ተይዞ መመዝገቡ ተረጋግጧል፡፡

3.4.2 <u>ስጋት</u>፣

የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ እና የበጀት አጠቃቀም እንዲዛባ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

3.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት ለወጪው በጀት መያዙንና በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ለመያዛቸው ማረጋገጥና መከታተል ያስፈልጋል፡፡

3.4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ፣

- በኮድ 6116 ለሠራተኞች ጥቅማ ጥቅም የሚውል በባንክ ወጪ ማመሳከሪያ ቁጥር 141190 ብር 280,040 ለመምህራን ኤክስቴንሽን ክፍያ መከፈሉን ጠቅሰው ሠነዱ ሲዘጋጅ በትክክል ሆኖ ወደ ወጪ ማመሳከሪያ (payement voucher) ሲመዘገብ 6116 የነበረው ኮድ ወደ 6216 በመመዝገቡ የተፈጠረው ብቃት ያለው ባለሙያ ዕጥረት የፈጠረው በመሆኑ በቀጣይ ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይደገሙ አንዱ ያዘጋጀውን ሌላው እንዲያመሳክረው የፕሮግራም፣ የሂሣብ መደብ ኮድ ስህተት እንዳይፈጠር በበጀት ቁጥጥሩ ሥር እንዲያልፍ እንዲቆጣጠር በተያዘው

2010 በጀት ዓመት ማስተካከያ ማድረግ መጀመራቸውን በምላሻቸው አሳውቀዋል፡፡

4. ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

4.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/4 የተሰብብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳቦች ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት የዩኒቨርሲቲው የተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ሂሳብ ውስጥ በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደና ከ1 ወር እስከ 3 አመት በተሰብሳቢነት የቆየ ብር 3,298,500.98 ቅድሚያ ክፍያ የተገኘ ሲሆን ይህም፣

- በሂሳብ መደብ 4201 የተየዘ ብር 2,539,547.22፣
- በሂሳብ መደብ 4203 የተያዘ ብር 71,976.28፣
- በሂሳብ መደብ 4210 የተያዘ ብር 480,771.03 እና
- በሂሳብ መደብ 4211 የተያዘ ብር 206,206.45፣ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

4.2 ስጋት፣

ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በጊዜው ሳያወራርዱ ማቆየት የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ዓመታዊ ሂሳቡን በወቅቱ ዘግቶ ሪፖርት እንዳያቀርብ ከማድረጉም በላይ በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በፋይናንስ መመሪያው መሠረት ወጪ የተደረጉ ቅድሚያ ክፍያዎች የሚወራረዱበትን ስርአት በመዘርጋት እና ለግዥ ሠራተኞች የሚሰጡ ቅድሚያ ክፍዎች በቅድሚያ የተሰጠ ክፍያ ሳይወራረድ ተጨማሪ ሠነድ እንዳይሰጥ ጥንቃቄ በማድረግ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይወራረዱ ለበርካታ ጊዜ እንዳይቆዩ መደረግ አለበት፡፡

4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ፣

- በሂሳብ መደብ 4201 ተሰብሳቢ ሂሣብ ከ2007 ዓም ጀምሮ የተመዘገቡ ሲሆን ተቋሙ ትኩረት ሰጥቶ በተቀጽላ ሌጀር የተከፈተላቸው ግለሰቦች በሠነድ ወይም በጥሬ ተመላሽ እንዲያደርጉ ከወር ደመወዝ መቀነስ የጀመረ ሲሆን ተቋሙን ለቀው

የወጡትን ደግሞ በደብዳቤ በክትትል ላይ ሲሆን በቀጣይ በማያቀርቡት ላይ ጉዳዩን አጣርቶ ለህግ የሚያቀርብ እንደሚሆን፣

- በሂሳብ መደብ 4203 በ2008 ለሰራተኞች ቅድመ ክፍያ ብድር የተሰጠ በመሆኑ ይህም ከወር ደመወዝ ተቀናንሶ ገቢ እየተደረገ ሲሆን ተቋሙ የሌሉትን በደብዳቤ እየጠየቀ እንደሚገኝ፣
- በሂሳብ መደብ 4210 በተቋሙ ከፍተኛ የውሃ አቅርቦት ችግር በመኖሩ ከክልሉ ውሃ ፍሳሽ ጋር በመሆን ከከተማው እስከ ተቋሙ ድረስ ለውሃ ዝርጋታ የተከፈለ ሲሆን፤ ሌሎች የተቋሙን ገንዘብ ለማስመለስ የፍርድ ቤት ፋይል መክፈቻ የተከፈለ ሲሆን የፍርድ ቤት ውሳኔ እንዳገኘ የማስተካከያ ምዝገባ የሚደረግ መሆኑን፣
- በሂሳብ መደብ 4211 የተያዘው የግዥ ባለሙያዎች ውስን በመሆናቸው ወጪ ያደረጉትን ሳያወራርዱ ለአስቸኳይ ግዥ ስለሚታዘዙ በወቅቱ ባለማወራረዳቸው እና በወሰዱት ገንዘብ ልክ ደረሰኝ ያለማቅረብ ችግር የሚታይ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ እንዲያወራርዱ ተቋሙ ወርሃዊ ደመወዝ የያዘበት እና ተመላሽ እየተደረጉ እንደሚገኝ፣

በአጠቃላይ በተሰብሳቢ የተያዙ ወጪዎች ትኩረት ሰጥተው ያደረጉትን ማስተካከያ ሪፖርት የሚያቀርቡ መሆኑን፣ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

5. <u>ተከፋይ ሂሳብ</u>፣

5.1 <u>ግኝት</u>፣

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5/ሀ እና መ ማንኛውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበትና ለእያንዳንዱ ተከፋይ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተከፍቶለት ክትትል መደረግ እንዳለበት ተገልጿ፡፡

በዚህ መሠረት የዩኒቨርሲቲው ተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ ከሚታይ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደና በሂሳብ መደብ 5004 የተያዘ ብር 3,124,164.23 መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

5.2 <u>ስጋት</u>፣

ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ ዩኒቨርሲቲው በበጀት ዓመቱ ለመሥራት ያቀደውን በመተው ከባለፈው ዓመት የዞረውን ዕዳ በመክፈል በዕቅድ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥርበታል፡፡

5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዩኒቨርሲቲው ያለበትን ዕዳ በመክፈል ከዕዳ ነጻ መሆን ያለበት ሲሆን ለወደፊቱ ክፍያዎች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲከፈሉ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- በሂሳብ መደብ 5004 የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ከ2007 ዓ.ም ለሠራተኞች ወርሃዊ ደመወዝ በአግባቡ የከፈለ ሲሆን ሠራተኞች በዝውውር፤ በቅጣት ሣይከፈላቸው የቀረ አቤቱታ ያላቀረቡ ሲሆን ወቅቱ ከፔሮል መሰረዝ እና ማስተካከያ ማድረግ ሲገባ በተቋሙ ውስጥ በቂ ባለሙያ ባለመኖሩ በየወሩ ምዝገባው ሣይስተካከል መቅረቱን፣ በመሆኑም በእርጅና ጊዜ መግለጫ (Aging analysis) ላይ የማይከፈል የሠራተኛ ወርሃዊ ደመወዝ እንዲሰረዝ ለፌዴራል ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ማሳወቃቸውን፣ ለወደፊቱ በየወሩ ደመወዝ የማይከፈላቸው ሠራተኞች ከፔሮል በመሰረዝ እና በቅጣት የማይከፈላቸው ሠራተኞች የማስተካከያ ምዝገባ እንደሚያደርጉ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

6. የበጀት ሂሳብ፤

6.1 ግኝት፤

በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡

በዚህ መሰረት በ2009 በጀት ዓመት ለዩኒቨርስቲው የተመደበ የተስተካከለ በጀትና ሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲመዛዘን፣

የወጪ ሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት (2)	ሥራ ላይ የዋለ በጀት (1)	ልዩነት በገንዘብ (2-1)	ልዩነት በ% (2-1)/2 *100
	ከበጀት በላይ የወጣ (መደበኛ)			
6111	28,906,980.00	32,275,440.94	3,368,460.94	11.65
6113	771,160.00	1,447,302.15	676,142.15	87.68
6121	7,891,580.00	13,377,538.15	5,485,958.15	69.52
6123	-	387,440.33	387,440.33	
6131	2,898,500.00	3,098,259.86	199,758.86	6.89
6133	95,310.00	155,868.09	60,558.09	63.54
6212	1,916,750.00	2,002,060.20	85,310.20	4.45

6218	**1,400,000.00**	**1,425,497.92**	**25,497.92**	**1.82**
6219	**510,480.00**	**909,430.89**	**398,950.89**	**78.15**
6232	**1,580,450.00**	**1,670,914.04**	**90,464.04**	**5.72**
6233	**1,283,420.00**	**1,397,122.54**	**113702.54**	**8.86**
6256	**-**	**59,973.52**	**59,973.52**	
6258	**100,000.00**	**225,680.45**	**125,680.45**	**125.68**
6259	**610,000.00**	**706,675.40**	**96,675.40**	**15.85**
6313	**5,753,500.00**	**30,671,655.50**	**24,918,155.500)**	**11.65**
ድምር	**53,718,130.00**	**89,810,859.98**	**36,092,729.98**	**67.19**
		ያልተሠራበት በጀት (መደበኛ)		
6112	**245,510.00**	-	245,510.00	100.00%
6114	**500,000.00**	347,712.50	152,287.50	30.46%
6211	**1,316,000.00**	514,997.36	801,002.64	60.87%
6213	**1,432,250.00**	309,593.57	1,122,656.43	78.38%
6214	**475,000.00**	344,792.80	130,207.20	27.41 %
6216	**18,000,000.00**	11,286,350.37	6,713,649.63	37.30%
6217	**1,849,200.00**	1,381,883.98	467,316.02	25.27 %
6221	**890,000.00**	-	890,000.00	100.00 %
6222	**110,000.00**	25,700.84	84,299.16	76.64%
6223	**3,649,760.00**	1,610,810.42	2,038,949.58	55.87 %
6231	**2,973,770.00**	2,463,621.70	510,148.30	17.15%
6243	**613,000.00**	24,171.98	588,828.02	96.06%
6244	**601,000.00**	157,096.88	443,903.12	73.86 %
6245	**263,440.00**	78,116.70	185,323.30	70.35%
6251	**2,022,890.00**	1,270,068.28	752,821.72	37.22%
6252	**1,181,460.00**	59,704.00	1,121,756.00	94.95%
6253	**283,000.00**	199,802.01	83,197.99	29.40%
6254	**700,000.00**	336,264.45	363,735.55	51.96 %
6255	**225,000.00**	15,153.15	209,846.85	93.27 %
6257	**500,000.00**	151,028.15	348,971.85	69.79%
6271	**1,755,340.00**	1,494,585.32	260,754.68	14.85 %
6323	**790,000.00**	691,682.79	98,317.21	12.45%
6412	132,710.00	20,000.00	112,710.00	84.93%
6414	100,000.00	-	100,000.00	100.00%
6417	839,000.00	352,386.81	486,613.19	58.00 %
6419	900,800.00	35,000.00	865,800.00	96.11%
ድምር	**42,349,130.00**	**23,170,524.06**	**19,178,605.94**	

- ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 36,092,729.98 በወጪ ሂሳብ መደቦች 6111፣ 6113፣ 6121፣ 6123፣ 6131፣ 6133፣ 6212፣ 6218፣ 6219፣6232፣ 6233፣ 6256፣ 6258፣ 6259 እና 6313 የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ለበጀት

ዓመቱ ከተመደበው የተስተካከለ በጀት በላይ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ፣ ከዚህ ውስጥ በወጪ ሂሳብ መደብ 6123 የወጣ ብር 387,440.33 እና በወጪ ሂሳብ መደብ 6256 የወጣ ብር 59,973.52፣ በድምሩ ብር 447,413.85 አስቀድሞ በጀት ባልጸደቀባቸው /ባልተፈቀደባቸው ወይም በጀት በሌላቸው/ የወጪ ሂሳብ መደቦች ወጪ የተደረገ መሆኑ፣

- ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 19,178,605.94 በወጪ ሂሳብ መደቦች 6112፣ 6114፣ 6211፣ 6213፣ 6214፣ 6216፣ 6217፣ 6221፣ 6222፣ 6223፣ 6231፣ 6243፣ 6244፣ 6245፣ 6251፣ 6252፣ 6253፣ 6254፣ 6255፣ 6257፣ 6271፣ 6323፣ 6412፣ 6414፣ 6417 እና 6419 ከተመደበው የተስተካከለ በጀት ከ10% በላይ ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣ ተረጋግጧል፡፡

6.2 <u>ስጋት</u>፣

- የበጀት ዝውውር ሣይደረግ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም እንዲሁም በጀት በሌለው የወጪ ሂሳብ መደብ ወጪ ማውጣት ህግን ከመጣሱ ባሻገር መንግሥት ያለውን ውስን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- ዩኒቨርሲቲው የታወጀለትን በጀት በወቅቱ አለመጠቀሙ ሊደርስበት ካቀደው ግብ እንዳይደርስ ከማድረጉም በላይ የሀገሪቱንም ውስን ሃብት ያለጥቅም እንዲቀመጥ ሊያደርገው ይችላል፡፡

6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በቂ በጀት መኖሩን የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር ካርድ በማቋቋም ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውንም የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፡፡

6.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የሥራ አመራሩ፣

- በ2009 ዓ.ም ለተቋሙ መምህራን ከሀምሌ ወር 2008 ጀምሮ የደሞዝ ጭማሪ መንግስት በማድረጉ እንዲሁም ለመንግስት ሠራተኞች ከጥር 2009 ዓ.ም የደመወዝ ማስተካከያ በመደረጉ ምክንያት ከዕቅድ ውጪ በመከፈሉ፣

- ተቋሙ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሲቋቋም ከዛሬ 10 ዓመት በፊት ለ400 የግብርና ኮሌጅ ተማሪዎች ማሰልጠኛ የተሰራ ሲሆን ያረጀና ወቅታዊ ጥገና ያልተደረገለት፣ በቂ ፈርኒቸር የሌለው በመሠረተ ልማት ያልተደራጀ በመሆኑ አስገዳጅ ወጪ ማለትም የተማሪዎች አልጋ፤ የቂም ሣጥንና ወንበር፤ የተማሪዎች መማሪያ ክፍል እና መመገቢያ፣ በመማር ማስተማር የትምህርት ቁሳቁስ፤ የኮምፒውተር፤ ፕሪንተሮች፤ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ወዘተ… በዕቅድ ቢካተቱም ለተቋሙ ከተያዘው ዕቅድ በላይ አስገዳጅ ወጪ በማጋጠሙ ምክንያት ሣይካተቱ መቅረታቸውን፣
- ከጋምቤላ ክልል የአየር ፀባይ የተነሣ በምግብ ዙሪያ በአካባቢው የጤፍ፤ የአትክልትና የጥራጥሬ ምግቦች የማይመረቱበት ሲሆን ከሌላ አካባቢ የተለየ ጭማሪ በመታየቱ፤ በከተማ ውስጥ የውሃ አቅርቦት በቂ ባለመሆኑ በየቀኑ ለሚገዛው የመጠጥ ውሃ ክፍያ፤ ለተማሪዎች ምግብ ዝግጅት የማገዶ ግዥ የሚወጡ ክፍያዎች አካባቢው በወባ ከመጠቃቱም ጭምር እጅግ አስገዳጅ የሆኑ ወጪዎች የተስተናገዱበት ሲሆን፣ የሂሳብ መደብ ኮድ ከበጀት በላይ በማኔጅመንት ውሣኔ ተወስኖ የተጠቀሙ መሆኑ፤ በተጨማሪም በተቋሙ በበጀት ላይ ይሰራ የነበረ አንድ ባለሙያ ለመ/ቤቱ ሳያሳውቅ ከሥራ ቦታ በመጥፋቱ እና ይህንን ተከትሎ ከነበረው የባለሙያ ዕጥረትና የማስፈጸም አቅም ውስንነት አጠቃላይ በሂሳብ አሰራራቸው ላይ የተነሳ በዕቅድ ያልተያዙ ክፍያዎች በጀት ዝውውር ሲደረግ ለፋይናንስ ክፍሉ ግልባጭ በለመደረጉ ዝውውሩ ወደ አይቤክስ ባለመመዝገቡ ጭምር መሆኑን፣
- በመሆኑም ከ2009 ዓ.ም የበጀት አጠቃቀማቸው ከፍተኛ ልምድ ስላገኙ በተያዘው በጀት ዓመት የበጀት ተቆጣጣሪ ተመድቦ የፋይናንሱን ሥራ ከወዲሁ ከበጀት በላይ እና በታች እንዲቆጣጠር በመሰራት ላይ እንደሚገኝ፣ ይሁን እንጂ የበላይ አካል ይህንኑ ችግራቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ወቅታዊ ድጋፍና ክትትል እንዲያደርግላቸው አቅማቸውም እንዲገነባ በማለት በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

6.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በተለይ ወጪ ከበጀት በላይ እንዳይወጣ ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ ወይም በዝውውር ማስተካከል ሲገባ በምላሹ እንደተገለጸው በማኔጅመንት ውሣኔ ከበጀት በላይ መጠቀም አግባብነት ስለሌለው ለወደፊቱ በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት መሠራት አለበት፡፡

7. <u>ንብረት፣</u>

7.1 <u>ቋሚና አላቂ ዕቃዎች፣</u>

7.1.1 <u>ግኝት፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር649/2001 እና በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተገለፁት ሁኔታዎች እና ድንጋጌዎች መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

<u>በዕቃ ግምጃ ቤት</u>

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂና የቋሚ ንብረቶች ከወጪ ቀሪ ቆጠራ (Inventory) ያልተደረገ መሆኑ፤
- በዩንቨርሲቲው የአላቂ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ቋሚ እቃዎች፣ በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አላቂ እቃዎች የሚገኙ መሆናቸዉ፣
- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ አገልግሎት አይሰጡም ተብለዉ የተመለሱ የተለያዩ ላፕቶፖች (ብዛት 5) ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸዉ፣
- በዩኒቨርሲቲ ግቢ ዉስጥ ወደ ምግብ ቤት አከባቢ ያለአገልግሎት የተቀመጠ ጄኔሬተር መኖሩ፣
- በንብረት ስቶር ዉስጥ መወገድ የነበረባቸው ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ የተለያዩ የመኪና ጎማዎች ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆናቸዉ፣ በዩኒቨርሲቲ ግቢ ዉስጥ የተለያዩ ቦታዎችና ወደ ምግብ ቤት አከባቢ መወገድ የነበረባቸው ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ የብረት አልጋዎች፣ሳጥኖች፣ቆርቆዎች እና ወንበሮች ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆናቸዉ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

7.1.2 <u>ስጋት</u>፣

ዩኒቨርሲቲዉ የንብረት አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና አጠባበቅ በመመሪያው መሠረት ተፈፃሚ ካልሆነ በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጡ ይችላል፡፡

7.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

የዩንቨርሲቲውን ንብረት ከጥፋትና ከብክነት ለመከላከል ይቻል ዘንድ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ከላይ በተዘረዘሩት የቁጥጥር ድክመቶችና የአሰራር ክፍተቶች ላይ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

7.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የሥራ አመራሩ ምግብ ቤት አከባቢ ያለአገልግሎት ስለተቀመጠው ጄኔሬተር ምላሽ ያልሰጡ ሲሆን፣

- በበጀት ዓመቱ የቋሚና አላቂ ንብረቶች ቆጠራ የተጠናቀቀ ቢሆንም በየቢሮ ያሉት ንብረቶች ያላለቁ በመሆኑ በቀጣይ በፍጥነት የሚሄዱበት እንደሚሆን፣
- ተቋሙ የራሱን አዲስ ግንባታ ያልጨረሰ በመሆኑና በአሮጌ ህንጻ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ በቂ መጋዝን ካለመኖር ጋር ተያይዞ የተፈጠረ በመሆኑ በቀጣይ ቋሚ እና አላቂ እንዲሁም አገልግሎት የሰጡትን የመለየት አሰራር የሚቀጥልና አፈጻጸሙን ሪፖርት የሚያደርጉ መሆኑን፣
- በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት አገልግሎት የማይሰጡ በቁጥር 05 ላፕቶፕ አሉ የተባለዉ እነዚህን ላፕቶፖች በትንሽ ብልሽት የቆሙ ስለሆነ ለጥገና የተቀመጡ እንጂ የሚወገዱ ባለመሆናቸው በአስቸኳይ አስጠግነው ወደ ሥራ የሚያስገቡ መሆናቸውን፣
- አገልግሎት የሰጡ የተለያዩ የመኪና ጎማዎች በስቶር ዉስጥ የተገኙት የኢፌዲሪ የመን/ግዥ ንብ/ማስወገድ አገልግሎት የሚወገዱበትን ሂደት በደብዳቤ የጠየቁና ምላሹን እንዳገኙ የሚያስወግዱ መሆናቸውን፣
- በምግብ ቤት አካባቢ የሚገኙትን አልጋዎችና ሌሎች ብረታብረቶች በተመለከተ እንዲወገዱ ለብቻቸዉ የሰበሰቧቸዉ ስለሆነ በቅርብ ቀን በተቋቋመዉ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ የሚወገዱ እንደሆነ፣ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

7.2 <u>የተማሪዎች ክሊኒክ</u>፣

7.2.1 <u>ግኝት</u>፣

የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ክሊኒክ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የመድሃኒት አያያዝና አጠባበቅ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተገለፁት ሁኔታዎች እና ድንጋጌዎች መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

- በተማሪዎች ክሊኒክ ስቶር ገቢና ወጪ ለሚደረጉ መድሃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- በበጀት አመቱ መጨረሻ በተማሪዎች ክሊኒክ ስቶር እንዲሁም በህክምና መስጫ የሚገኙ መድሃኒቶች ቆጠራ እና ከወጪ ቀሪ የሚያሳይ ሪፖርት (reconciled report) የሌለ መሆኑ፤
- በዕርዳታ የተገኙ የቲቢና የወሊድ መከላከያ መድሃኒቶች ዋጋቸዉ ሳይጠቀስ ገቢ የሚደረጉ መሆኑ፤

- በተማሪዎች ክሊኒክ ውስጥ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸዉ መድሃኒቶች ሳይወገዱ ተከማችተዉ የተቀመጡ መሆኑ፣ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

7.2.2 <u>ስጋት፣</u>

- ለመድኃኒቶች ገቢና ወጪ መከታተያነት ሞዴል 19 እና 20ን ጨምሮ ተገቢውን ምዝገባ አለማድረግ እንዲሁም በተወሰነ ወቅት ቆጠራ በማድረግ ከወጪ ቀሪውን የሚያሳይ ሪፖርት (reconciled report) አለማዘጋጀት የከወጪ ቀሪውን ትክክለኛነት ለማወቅ አያስችልም፡፡ የጠፋ ወይም የጎደለ መድኃኒት መኖሩን ለማወቅም አያስችልም፡፡
- በዕርዳታ የተገኙ መድኃኒቶችን በዋጋቸው መጠን ገቢ አለማድረግ መድኃኒቶቹ ቢጠፉ ለመከታተልና ለማስመለስ አያስችልም፡፡
- የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸዉ መድሃኒቶችን አለማስወገድ በአጋጣሚ ሊፈጠር በሚችል የአሠራር ስህተት ጤና ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

7.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከላይ በተመለከቱት ክፍቶች ላይ በተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መሰረት የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

7.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የሥራ አመራሩ፣

- የተባሉ ስህተቶችን አርመው ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ ከሚቀጥለዉ ጊዜ ጀምሮ ለማስተካከል ካሁኑ ወደ ሥራ መግባታቸውን፣
- በቀጣይ ጊዜ ሳይሰጥ ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 በመግዛት ጥቅም ላይ እንደሚያውሉ፣
- በዕርዳታ የሚመጡ መድሀኒቶች ከነዋጋቸዉ ስለሚመጡ ዋጋቸዉ ሞዴል 22 ላይ ተሞልቶ ወጪ በማድረግ እንዲስተካከል እንደሚደረግ፣
- በአጠቃላይ የመድሀኒት ማከማቻ በጤና ባለሙያ ቢሠራ ጥሩ ቢሆንም የባለሙያ አረጥረት በመኖሩ ወደፊት ሊስተካከል እንደሚገባዉ አቅጣጫ መያዙን፣
- በክሊኒኩ ጊዜ ያለፈባቸዉ መድሀኒቶች በተለያየ ምክንያት እስከዛሬ ለብቻዉ ተከማችተዉ በአንድ ክፍል ያሉትን በቀጣይ አስወገጅ ኮሚቴ አዋቅረው ተግባራዊ በማድረግ ሪፖርት የሚያደርጉ መሆኑን፣ ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

7.2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በዕርዳታ የሚመጡ መድሀኒቶች ወጪ ሲደረጉ የመጡበት ዋጋቸው ሞዴል 22 ላይ ተሞልቶ መጪ መደረጋቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ወጪ ከመደረጋቸው በፊት በመጡበት ዋጋ በሞዴል 19 ገቢ መደረግ አለባቸው፡፡

7.3 <u>የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ</u>፣

7.3.1 <u>ግኝት</u>፣

በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ዓ.ም ክፍል ሁለት አንቀፅ 6/1 ላይ እንደተመለከተው የመንግሥት መ/ቤት በግዥ፣ በስጦታ፣ በዝውውር…ወዘተ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መዝግቦ መያዝ እንዳለበት ይገላፃል፡፡ የዚሁ መመሪያ ክፍል 3 አንቀጽ 9/1 እና 9/2 መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተል እና መዝግቦ ለመያዝ እንዲረዳቸው የተሽከርካሪዎች የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ እንዳለባቸውና እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ መጠን ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

ከላይ በተገለጸው መመሪያ መሰረት የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪ መኪናዎች በኦዲት ሲታዩ፣

- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-08711 Mercedes Bus እና የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-05683 ኤኔትሬ፣ በድምሩ 2 ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ መከታተያ የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ እና ተሽከርካሪዎቹ በሂዱበት ኪ/ሜ ተገምቶ ነዳጅ የሚሞላላቸው መሆኑን፣
- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-05683 ኤኔትሬ (**እላይ ጌጁ የማይሠራ የተባለ**) እና ሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-16861 ኒሳን ፣ በድምሩ 2 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑን፣

በኦዲት ቅኝት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

7.3.2 <u>ሥጋት</u>፣

- የሊብሬው አለመኖር የተሽከርካሪዎቹን ባለቤትነት ጥያቄ ውስጥ ሊከት ይችላል፡፡
- የጌጁ አለመስራት ለነዳጅ ግዥ ወጪ የሆነ የመንግሥት ገንዘብ እንዲመዘበር በር ይከፍታል፡፡ በተጨማሪም በመንግስት ውስን ሃብት የተገዙ ንብረቶች ለብክነት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

7.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

- ሊብሬ ለሌላቸው ከሚመለከተው አካል/ክፍል/ ሊወጣላቸው /ሊቀርብላቸው/ ይገባል፡፡
- ጌጃቸው የተበላሹ ተሽከርካሪዎች ለምንና እንዴት እንደተበላሹ ተጣርቶ ሊጠገን ወይም ሊቀየርላቸው የሚገባ ሲሆን የነዳጅ እደላ ስርዓት አንድ ተሽከርካሪ በሊትር በአማካይ በሚጓዘው ርቀት መጠን እየተለካ መሆን ይኖርበታል፡፡

7.3.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ፣

- ሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-08711 /Mercedes Bus/፣ እና ሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-05683 /ኤኔትሬ/፣ በድምሩ 2 ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ መከታተያ የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጅ በተመለከተ ማርቸዲሱ በ2009 የበጀት ዓመት ይኸው ችግር እንደነበረበትና በዚሁ ዓመት አዲስ አበባ ልከው ቢያሰሩም በቅርቡ የተበላሸ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ቆሞ ያለና በዚሁ በጀት ዓመት ቅድሚያ ለማሰራት በጨረታ ሂደት ላይ ያለ መሆኑ እና በሌላ በኩል ኤንትሬውን በተመለከተ ከቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር በዚሁ ባለበት መልኩ ለግብርና ኮሌጅ የተሰጠ በመሆኑና በክልሉ የኤንትሬ ጋራዥ የሌለና ወደ አዲስ አበባ እንዳይላክ አቅም የሌለው በመሆኑ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ጠይቀው እንዳገኙ ከመንግስት ግዢ አስ/እና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጋር በመወያየት መፍትሄ የሚፈልጉ እንደሆነ፣
- ሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-16861 ኒሳን፣ ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ዩኒቨርስቲው ከመከፈቱ ቀደም ብሎ ከመቱ ዩኒቨርስቲ የተሰጣቸው በመሆኑ ዩኒቨርስቲውን ጠይቀው በማኔጅመንት አስወስነው በቅርቡ እንደሚሰጧው የገለጹላቸው መሆኑን፣ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

8. <u>ልዩ ልዩ፤</u>

8.1.1 <u>ግኝት፤</u>

በዩንቨርሲቲዉ በጥበቃ፣ በግዥ፣ በንብረት ያዥነት እንዲሁም በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 አንቀጽ 7 መሰረት ዋስትና እንዲያቀርቡ መደረግ ሲገባ የተወሰኑት ያለምንም ዋስትና እየሰሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

8.1.2 <u>ሥጋት፤</u>

በመንግሰት ዉስን ሀብት ላይ ጥፋት ቢፈጸም ተጠያቂንቱን የሚወስድ አካል ላይኖር ይችላል፡፡

8.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በዩንቨርሲቲዉ ከላይ በተገለጹት የስራ መደቦች ላይ ተቀጥረዉ የሚሰሩ ሠራተኞች ዋስትና እንዲያቀርቡ መደረግ አለበት፡፡

8.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- የሥራ አመራሩ በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ በጥበቃ ስራ፣ በግዥ ሥራና በገንዘብ ያዥነት ስራ ላይ ተሰማርተው ከሚሰሩ ሰራተኞች እስካሁን ዋስትና ያላቀረቡ ሁለት ሰራተኞች ዋስትና እንዲያቀርቡ በደብዳቤ ያሳወቁ በመሆኑ በቀጣይ አፈጻጸሙን ሪፖርት የሚያቀርቡ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

8.2.1 <u>ግኝት፣</u>

የፌዴራልመንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 8/2 የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፤ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች የማደራጀትና በቂ የትምህርት ዝግጅትና አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያካበተ የውስጥ ኦዲት ኃላፊ የመመደብ የመ/ቤት የበላይ ሃላፊ ሃላፊነት እንደሆነ ይገልፃል፡፡

በዚህ መሠረት የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የሰው ኃይል ሁኔታ ሲታይ፣ ለዳይሬክቶሬቱ 10 ኦዲተሮች የሚያስፈልጉ ቢሆንም ለክፍሉ አንድ ኦዲት ዳይሬክተር እና አንድ የፋይናንስ ኦዲት ቡድን መሪ ባለሙያዎች ብቻ የተቀጠሩ ሲሆን በ8 ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኛ ያልቀጠረ በመሆኑ 80 በመቶ የክፍሉ የሰው ኃይል ያልተሟላ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

8.2.2 <u>ሥጋት፣</u>

የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በበቂ የሰው ሃይል ካልተደራጀ ተግባርና ኃላፊነቱን ላይወጣ ይችላል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትም ፍተሻም ደካማ ሊሆን ይችላል፡፡

8.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ክፍሉ በመዋቅሩ መሠረት ተገቢውን የሙያ ብቃት፤ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

8.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ፣

- ዩኒቨርሲቲው አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከ2007 ዓ.ም በጀት ዓመት ጀምሮ ወቅቱን ጠብቆ የኦዲት ሥራ ለማሰራት በክልሉ ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ቢወጣም ባለሙያ ማግኘት አለመቻሉን፣
- ይህንኑ ችግር ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የገን/ኢ.ኮ/ት-ብ/ሚኒስቴርና ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፐብ/ሰር/የሰው ኃብት ልማት ሚኒስቴር ያሉትን ክፍት መደቦች ከማሳወቅ በተጨማሪ ከማዕከል ባለሙያ እንዲቀጠርላቸው የጠየቁ ቢሆንም እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ባለመሳካታቸው ከክልሉ ባለሙያ አዛውሮ ለማሰራት የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ ላይ የሚገኙ ሲሆን የዘለቄታ መፍትሄ እንዲያገኙ የሚመለከታቸው አካላትም ይህንኑ በተቋማቸው ላይ ያለውን ዘርፈ ብዙ የባለሙያ ችግር ተገንዝቦ መፍትሄ በማፈላለጉ የበኩሉን ድጋፍ ያደርግላቸው ዘንድ እየጠየቁ ከሁሉ አስቀድመው ያሉባቸውን ክፍተቶች በማሳየት እንዲማሩበት አየተደረገ ላለው ሂደት እጅግ ላቅ ያለ ምስጋና ለማቅረብ እንደሚወዱ፣ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

8.3.1 <u>ግኝት</u>፣

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል ሁለት አጠቃላይ ደረጃዎች አንቀጽ 6/5 የሥራ አመራሩ በስጋት ተጋላጭነት ላይ ተገቢና ተስማሚ እርምጃ መውሰድ እንዲችል በመስሪያ ቤቱ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ላይ የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ በየጊዜው መደረግ እንዳለበት ይገልፃል፡፡
ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲው ለተልዕኮው መሳካት በሚያከናውናቸው ቁልፍ ተግባሮች ላይ በመመርኮዝ እና በሚያከናውናቸው የዕለት ተዕለት ሥራዎች ውስጥ እንደ ግዥና ንብረት አስተዳደር፣ ፋይናንስ አስተዳደር፣ ምግብ አገልግሎት፣ ነዳጅ እደላ እና በመሳሰሉት ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶችን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚረዱ የአሰራር ስልቶችን በመቀየስ የዩኒቨርሲቲውን የስጋት ተጋላጭነት አስተዳደር ዕቅድ /Risk Management Plan/ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

8.3.2 <u>ሥጋት</u>፣

- ሊያጋጥሙ /ሊደርሱ/ የሚችሉ አደጋዎችን /ጥፋቶችን/ አስቀድሞ መከላከል አያስችልም፡፡
- የዩኒቨርሲቲው የመልካም አስተዳደር ግንባታ እንዲሁም የመንግስት ንብረት እና ገንዘብ ለብልሹ አሰራር ሊጋለጥ ይችላል፡፡

8.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ዩኒቨርሲቲው ለተልዕኮው መሳካት በሚያከናውናቸው ቁልፍ ተግባሮች ላይ በመመርኮዝ እና በሚያከናውናቸው የዕለት ተዕለት ሥራዎች ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶችን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚረዱ የአሰራር ስልቶችን በመቀየስ የስጋት ተጋላጭነት አስተዳደር ዕቅድ ሊኖረው ይገባል፡፡

8.3.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የሥራ አመራሩ፣

- የስጋት ተጋላጭነት አስተዳደር ዕቅድ /Risk Management Plan/ ለብቻው ባይዘጋጅም በዋናው ዕቅድ ግዢዎች በቀጥታ እና በተፈቀደ መንገድ እንዲሆን የታቀደ መሆኑን፣ ንብረት አስተዳደር ገቢና ወጪ በተመለከተ እስከ ምክትል ፕሬዚዳንቱ የሚደርስ ፎርማት በመጠቀም የገቢ ወጪ አሰራር ክትትልና ቁጥጥር መኖሩ፣ በምግብ አገልግሎት በኩል የተማሪዎች አገልግሎት የተለያዩ ቁጥጥርና መከታተያ ፎርማት በመጠቀም ላይ እንዳሉ፣ ነዳጅ እደላ በኩፖን ሆኖ ከንብረት ክፍል አንስቶ ስምሪትን ጨምሮ ቅጽ በማዘጋጀት የቁጥጥር ስርዓት የሚጠቀሙ መሆኑን ጠቅሰው ባገኙት ግብረ መልስ መሠረት ለወደፊቱ ራሱን የቻለ ዕቅድ በማዘጋጀት የሚጠቀሙ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

9. <u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝትና የማሻሻያ ሀሳቦች፣</u>

9.1 <u>ግኝት፣</u>

- በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2(በ) መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በውጭ ኦዲት ወይም በውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተመለከተው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡
- በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሠረት ደግሞ ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው፣ እንዲሁም የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የጋምቤላ ዩኒቨርስቲ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ፤

- ለተሽከርካሪ ጥገና ለተከፈለ ብር 24,818.75 እና የጨፍ ዱቄት ለተገዛበት ብር 244,598.00፣ በድምሩ ብር 269,416.75 (24,818.75 + 244,598.00) ገንዘቡን ከተቀበሉ ድርጅቶች የቀረቡ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች ከወጪ ሰነዶቹ ጋር ያልተያያዙ መሆኑ፣
- በዩንቨርሲቲዉ በጥበቃ፣ በግዥ፣ በንብረት ያዥነት እንዲሁም በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች በመመሪያዉ መሰረት ዋስትና እንዲያመጡ ወይም እንዲያቀርቡ መደረግ ሲገባ ያለምንም ዋስትና እየሰሩ መሆኑ፣

በሚሉ ግኝቶች ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

9.2 ሥጋት፣

- በኦዲት ሪፖርት የማሻሻያ ሃሳብ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ እርምጃ አለመውሰድ የመንግስት ንብረት ለግለሰቦች መጠቀሚያ እንዲውል መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም በሌሎች ተጠቃሚዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር እና መንግስትን ለሌላ ተጨማሪ ወጪ ሊጋብዝ የሚችል ከመሆኑም ሌላ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡
- ነባር የአሠራር ክፍተቶች እንዲቀጥሉና ሌሎች አዳዲስ የአሠራር ክፍተቶች እንዲከሰቱ መንስኤ ሊሆን የሚችል ሲሆን ይህ ደግሞ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መጥፋትና መጉደል ሊዳርግ ይችላል፡፡

9.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- በኦዲት ግኝቶቹና የማሻሻያ ሀሳቦቹ ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ የሥራ አመራሩ፣ የዩኒቨርስቲው ቦርድና የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

9.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ፣

- በወቅቱ በበጀ/ፋይ/አስ/ እና በንብረት አስ/ የሥራ ቦታ ላይ የነበሩ ዳይሬክተሮች የብቃት ማነስ የሚታይባቸው መሆኑ በተረጋገጠው መሠረት ከቦታቸው እንዲነሱ የተደረገ ሲሆን ይህንን ተከትሎ የዕርምት ርምጃ ለመውሰድ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ እያለ በወቅቱ የነበረው የግዥ አስ/ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር መ/ቤቱን ለቆ ወደ ሌላ ክልል ሴክተር መ/ቤት በመዛወሩ እና ሰነዶቹን የማፈላለግ ሥራ የቀጠለ በመሆኑ እንደተገኘ ሪፖርት የሚያደርጉ እንደሆነ፣

- ከግኝቱ በኋላ በተጠቀሰው የበጀት ዓመት የተቀጠሩ ሰራተኞች ዋስትና እንዲያቀርቡ መደረጉን፣ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልክም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!